# ኢትዮጵያችን

*ወቅታዊ አተታ*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 6 ቁጥር 3.......................................................የካቲት 11 ቀን 2015 ዓ.ም.


## “ኦርቶዶክስን፣ ኢትዮጵያን የሚያፈርስ መርዝ?”

*“ኦርቶዶክስን የሚያፈርስ መርዝ ኦርቶዶክስ ውስጥ እንዳለ. . .ኢትዮጵያን የሚያፈርስ መርዝ በእኛው በኢትዮጵያውያን ውስጥ እንዳለ ተምረንበታል። ለምን እባብ ኖረ? ለምን እባብ መርዝ ይዞ ይዞራል አይባልም፤... ተፈጥሯል፤ ከመርዙ ጋር አለ። እንዳያጠቃን፣ እንዳያጠፋን መከላከል ነው።”* ጠ/ሚር ዶር ዐብይ አሕመድ የካቲት 9 ቀን 2015 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አባቶች መካከል የነበረውን አለመግባባት ለመፍታት የተዘጋጀ የውይይት መርሐ ግብር ላይ ከተናገሩት የተወሰደ። ድሮ ድሮ ጅራፍ ይባላል ዛሬ ግን እንደወቅቱ እናርገውና “ጥይት እራሱ ገሎ እራሱ ይጮኃል” ማለት ይህ ነው። ጎበዝ ማን ሆነና እባቡ? “ያደቀነ ሰይጣን ሳያቀስ አይለቅም” እንደሚባለው እኚህ ሰው እስኪቀስሱ ከጠበቅን ሀገርም፣ ኦርቶዶክስም አትኖርምና “ሳይቃጠል በቅጠል” እንባባል። ከዚህ በላይ ምንም ሊሉን አይገባምና ሰውየው ጤናቸው አጠራጣሪ ነውና “ሳይብስ ወደ ፀበል” ይወሰዱ።

ዐብይ አሕመድ ጥር 18 ቀን 2015 ዓ.ም. በቴሌቪዥን መስኮት ብቅ ብሎ ያላገጠባትን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንና የናቀውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ዳግም የካቲት 8, 9 ቀን 2015 ዓ.ም. በተደረገ ውይይት/ምክክር አላግጦበታል። የዶር ዐቢይ ኢትዮጵያ ዘረ አማራ የሌለበት ለመሆኑ ወያኔ/ህሓወት ሥልጣን በያዘ ማግስት በአርባጉጉና በደኖ በኦነግ የተጀመረው ጭፍጨፋ በተለያየ ጊዜ እና ሰዓት ለ27 ዓመታት ሲካሄድ ተጉዞ በብልጽግና አገዛዝ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ደርሷል። በወለጋ ያሉ አማሮች በሙሉ ተጨፍጭፈዋል ወይም ተፈናቅለዋል። አጣዬ ለሁለተኛ ጊዜ ወድማለች። የወሎ አማሮች የጥይት እራት ሁነዋል፣ የጎንደርና ጎጃም አማራን ጨምሮ ከህወሓት ጋር የተካሄደ ጦርነት ተብሎ በተነደፈ የጋራ ሤራ በሚሊየን የሚቆጠሩ አማሮችና የትግራይ ወጣቶች ተማግደዋል። ዛሬም የተቻላቸውን ያኽል እየተዋደቁና መስዋዕት እየሆኑ ይገኛል። የዐብይ ብልጽግና “ኦሮሚያ” ብሎ በሰየመው የትኛውም ክልል ያለ አማራ እየታረደ፣ እየተፈናቀለ፣ የተረፈውም እየተሰደደ በጫካና በዱሩ ለቀን ሙቀት፣ ለለሊት ብርድ የተጋለጠው በመቶ ሺህ የሚቆጠር ቤተሰብ ቀላል አይደለም።

የዶር ዐብይ/ብልጽግና ኢትዮጵያ በመጤ ሃይማኖት የተበረዘችና የተዳከመች፣ የተከፋፈለች ወይም ከነአካቴው የጠፋች ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን መፍጠር ነውና ለዚህ ደግሞ በከፋ መልኩ በአለፉት 5 ዓመት አገዛዙ ብቻ በርካታ ቤተክርስቲያናት በአገዛዙ ድጋፍና ትእዛዝ ተቃጥለው ወድመዋል፣ በርካታ ተዘርፈዋል፣ ቀሳውስቱና ምዕመናን እየተጋዙ፣ እየተደበደቡ ዛሬ ያለንበት የተዋሕዶ ኦርቶዶክስ መከራ ላይ እንገኛለን። ሻሸመኔ ለሁለተኛ ጊዜ አሰቃቂ ጭፍጨፋ አስተናግዳለች።

ኢሕአዴግ ከውጭ ኃይሎች ጋር የገነባውን የዐብይ/ብልጽግና አገዛዝ ኢትዮጵያ የሀገራችንን አኩሪ ታሪክ የሚቀብርና ጥላሸት ለመቀባት ትልሙ ያደረገ ለመሆኑ ትውልዱን በፈጠራ ታሪክ ለመበረዝ በአኖሌ ዓፄ ምንሊክን አኩሪ ታሪክ በጡት ቆራጭነት ተምሳሌትነት ሐውልት ያቆሙ የታሪክ ነቀርሳዎች ናቸው።

አማራውን ማጥፋት ወይም ቀጥቅጦ “ባሪያ” ማድረግ፣ ኦርቶዶክስ ሃይማኖትን ከነታሪኳ ማጥፋት፣ የዓፄ ምኒልክን ታሪክ መቅበር የዐብይ/ብልጽግና ኦሮሙማ ግብ ነውና የዚህ ተግባራዊነት መጨረሻው ምዕራፍ ላይ ጠቅላዩ ደርሷል።

የድፍረቱ ድፍረት የምክር ቤት አባላቱን ሰብስቦ "ከየትም አምጥቼ በምገነባው ፕሮጀክት ገንዘብ አያገባችሁም" ያለው የኦሮሙማ መሪ ኢትዮጵያን ለመበታተን ከማይተኙት ባዕዳን ኃይሎች በገፍ በሚቸረው ዶላርና የጦር መሣሪያ በተለይ አዲስ አበባ ላይ እያካሄድኩ ነው የሚለው ፕሮጀክቶች በሙሉ የሕዝብን ሀሳብ ወደ ልማት እየሳበ ለሚያልማት "ኦሮሚያ ዋና ከተማነት" አዲስ አበባን ወደፊት በሸገር/ፊንፊኔ ስም ቀይሮ የኦሮሚያ ዋና ከተማ የማድርግ ቅዠት ላይ ሌት ተቀን እየፈጋ ይገኛል። ለዚህ ደግሞ ስኬታማነት በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባና አካባቢው አማራ የሆነ ነዋሪ ቤት ያለምንም ጠያቂ እየፈረሰ ሙሉ ቤተሰብ አውላላ ሜዳ ላይ እየዩ እያሉ እንደሆን የምንሰማው፣ የምናየው የየቀን ተግባር ሁኗል። አንጠራጠር ይህ ደግሞ በቀጣይነት ሙሉ በሙሉ የአዲስ አበባን ነዋሪ እጅግ በሚዘገንን መልኩ በመጨፍጨፍ ኦሮሚያ የግዛቱ ዋና ከተማ አድርጎ ለመጠቅለል እና የኦሮሚያ ቻርተር ተግባራዊ ለማድረግ እየተገፋ ነውና ልብ ያልው ልብ ይበል።

ዛሬ በሀገሪቷ የውጭ ምንዛሪ ተሚጦ ማንኛውም የውጭ ምንዛሪ የሚጠይቅ የንግድ እንቅስቃሴ የተሰማሩ ሁሉ ለአለፉት አምስት ዓመት የቤት ኪራይ፣ የሠራተኛ ደሞዝ እና ዓመታዊ ግብር እየከፈሉ ለመቀመጣቸው በዘርፉ የተሰማሩት ድፍረቱ ኖሯቸው ድምፃቸውን ማሰማት ይጠበቅባቸዋል። ይህ በዚህ እያለ በ50 ሚሊየን ዶላር የሚገነቡ የተለያዩ በርካታ ፕሮጀክቶች፣ በቅርቡ የተፎከረለትና ሥራውም የተጀመረው የ50 ሚሊየን ዶላር የቤተ መንግሥት ግንባታ ጉዳይ ከየት ከሚገኝ ገቢ ነው ብንል? መልሱ "ዶ/ር ዐብይን አትፈታተነው ተብሏል" እንደሚሆን አንጠራጠር። በሀገራችን ወገኖቻችን ምግብ ለመመገብ እየተሳቀቁ አለበት ዘመን ላይ ደርሰናል። "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንዲሉ በምግብ እጦት ሚሰቃዩ ሕፃናት፣ አዛውንት እናት አባቶች በተጨማሪ በጤና እየታወኩ በ10 ሺዎች ለህክምና ወጪ ይጠየቃሉ።

ውድ ኢትዮጵያውያን! ሀገራችን ዛሬ እጅጉን አስከፊ አደጋ ላይ ደርሳለች። ኢትዮጵያ መሪ አገኘች ተብሎ በአብዛኞች ዘንድ የተጨበጨበለትና እልል የተባለለት ዐብይ አሕመድ ድብቅ መርዙን እየረጨ ይገኛል። የኦሮሚያ ተግባራዊነት ፍጻሜ ሀገር እና ሕዝብ እያጠፋ ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያችንን ሊበትናት የገደሉ ጫፍ ደርሷል። በእብሪትና በትዕቢት የተወጠረው የዶ/ር ዐብይ አገዛዝ ከነሙሉው አገዛዙና ባለሥልጣናቱ ካልተወገደ እንደተመኙት ሀገሪቷን ይበትኗታል፤ ሌላ ቢቀር ግን እጅግ የሚዘገንን ቁጥር የሚሰላ የሰው ልጅ ሕይወት ማጣታችን እንዳለ ሁኖ በእጥፍ ሊያጠፉን ተዘጋጅተዋልና ከሕዝብ ኃይል በላይ ያለው ፈጣሪ ነውና እስከዛሬ እያንጋጠጥን ያለቀው ከበቂ በላይ ነውና ሁሉም ዘር የራሱን ሕይወት ለማዳን "ሕይወት ለሀገር፣ ሕይወት ለሕዝብ" በማለት መጠራራትና መዘጋጀት እንዳለበት ልንጠቁም እንወዳለን።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ አባቶች ማንነታችሁና እምነታችሁ እጅግ አክብራችሁት በነበረው የትላንቱ ቅዱስ የዛሬው ዲቢሎስ ተደፍሯል፣ ተሰድባችኋል፣ ይባስ ብሎ እናንተው እንዳላችሁት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ልትዋረድ ነው። ይህንን ተግባር እያከናወነ ያለው በዶ/ር ዐብይ የሚመራው አገዛዝ ለመሆኑ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ፤ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊና ከኒዮርክና አካባቢው ሃገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፤ የካቲት 2 ቀን 2015 ዓ.ም. ኢኦተቤ ቲቪ፤ ወቅታዊ ጉዳይ ያሉት፡- ***"እነ ወንድም አካለወልድ የመንግሥት መሣሪያዎች ናቸው። መንግሥት ያዘዛቸው፣ ያደራጃቸው መሣሪያዎች ናቸው። ዋናውን የሚሠራው መንግሥት ነው። የፌደራል መንግሥትና የኦሮሚያ ክልል መንግሥት ነው የሚሠራው። . . .መንግሥት ስለሆነ የሚያካሂደው መንግሥት ሁለት እያለ የሚጠራው ቀልድ አይሠራም።እኛ አይደለንም ሰዎቹን የለየናቸው፤ እራሳቸው ናቸው እራሳቸውን የለዩት። የማሉትን መሃላ፣ ያጸደቁትን ሕግ፣ ሥልጣን የሰጣቸውን ቀኖና፣ ቤተክሲያን የሰጣቸውን ሥራና ሥልጣን አስተዳደራዊ ኃላፊነት ክደው ነው የሄዱት።..."*** መልዕክት ሁላችሁም ልብ ውስጥ ያለ ነውና ቀደም ሲል የጀመራችሁትን ምዕመናኑን ከፆምና ፀሎት በዘለለ መልኩ ለቤተክርስቲያኗ ህልውና "መስዋዕት እንሆናለን" ያላችሁት ቃል ገዢ ቃል ነውና ከፍ አድርጋችሁት መንግሥትን ሳይሆን ዲቢሎስን ለማሸነፍ "መስቀል ኃይላችን" ብላችሁ ከፍ ታደርጉት ዘንድ አምላክ ይጠብቅባችኋል። እውነት እውነት እንላለን <u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ መፍረስ ማለት ሀገር መፍረስ ማለት ነውና ይህ ፖለቲካ ሳይሆን "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚሃብሔር ትዘረጋለች" እያላችሁ ያስተማራችሁት ምላሽ እንዲያገኝ አምላክ አደራውን በእናንተ ሐዋርያቱ ላይ አሳድሯል።</u>

ለአለፉት 50 ዓመት በተለይ ከደርግ አገዛዝ  ጀምሮ ፓትሪያርክ ቢገደሉ በወያኔ/ህወሓት ቢሰደዱ በየወቅቱ የነበሩት የቅዱስ ሲኖዶስ አባቶች ፍርዱን ለአምላክ ሰጥታችሁ በየአድባራቱ አረንጓዴ፣ቢጫ፣ቀይ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ እያውለበለባችሁ ለሀገርና ለሕዝብ በአደረጋችሁት ያላሰለሰ ፆምና ፀሎት እዚህ የደረሰችው ቤተክሲያን በዚህ ዘመን እንደማትፈርስ በታላቅ ተስፋ የምንመሰክረው እምነታችሁ ቀልድ አይደለምና ነው። የአሁኑ ግን ለየት ይላል የኢትዮጵያ ትንሳዔ መዳረሻው ላይ የተለቀቀው ዳቢሎስ መሪ ሁኗልና ፈተናችሁ ከባድ፣ ሰማዕትነታችሁም ቀርቧል። ከምዕመናን ጋር ተጀምሮ የነበረውን "የጥቁር ቀን" ወደ "ቀይ ቀን" የሚቀየርበትን ዳቢሎስ ደምሥራችሁን በመበጣጠስ ተግባራዊ ሊያደርገው ፈልጎታልና ቤተክርስቲያኗን እና ምዕመናኑን ታድኑ ዘንድ ከአምላካችሁ ተነጋገሩ።በይቅርታ ለመንግሥትና ለኃጢያተኛው ሲኖዶስ የሰጣችሁት ዕድል በዳቢሎሱ ተሸጧል። እናንተስ እምነታችሁን ለአምላካችሁ ሰጥታችኋልና ደስ ይበላችሁ።

በሀገር ቤት በመንቀሳቀስ ላይ ያላችሁ የፖለቲካ ድርጅቶች የኢትዮጵያ ህልውና እጅጉን አደጋ ላይ መሆኑን ትገነዘባላችሁ። ለመስዋዕትነት የተዘጋጀ መሪ ነው ሕዝብን ሊያንቀሳቅስ የሚችለው እና ከቅዱስ አባቶቻችን የሰሞኑ ጥንካሬ ነው ምዕመናኑን ዳር እስከዳር ያንቀሳቀሰው።ሕዝባችን ግምባሩን ለጥይት ሊሰጥ የተዘጋጀ ፊት መሪ ይፈልጋሉና ሀገር እንድትኖር ማንነታችሁን ምታሳዩበት ወቅት ፈለጋችሁትም አልፈለጋችሁ ነባራዊ ሁኔታውን ለገመገመ ደጃፋችሁ ላይ በራችሁን እያንኳኳ ነው። የዛሬ ሦስት ዓመት ዶ/ር ዐብይን/ብልጽግናን "በምርጫ እንዘርራለን" ተስፋ ባይጠላም ግና እውን ሀገር የኦሮሚያ ሁና ልትበታተን አገዛዙ ፈልጎታልና ያንዣበበው ቀውስ የቀናትና የወራት ሊሆን እንደሚችል ተገንዘቡት። የሰሞኑ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቅዱስ ሲኖዶስ መሪነት በመላው ዓለም ያሉ ምዕመናን ዳር እስከዳር በመንቀሳቀሳቸው ነው አገዛዙ የሚይዝ የሚጨብጠውን ያጣው። ይህ እንቅስቃሴ ደግሞ በመፈናቀል፣ በረሃብ፣ በደሞዝ ማነስ፣ በጥቅሉ በአገዛዙ የተማረረው ሕዝብ የተከማቸ ብሶት ውጤት ከእምነት ጋር እንደተጣመረ ለፖለቲከኞቻችን የሚዘነጋ አይመስለንም።

ከጥር 18ቱ የቅዱስ ሲኖዶስ እንቅስቃሴ ጀምሮ እስከዛሬ ከወትሮው በከፋ መልኩ በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች፣ በርካታ የቤተክህነት ወገኖች በየእሥር ቤቱ እየታጎሩ እንደሚገኙ ይታወቃል። በቀጣይነት በዛሬው የካቲት 10 ቀን 2015 ዓ.ም. የቅዱስ ሲኖዶስ መግለጫ መሰረት ቀጣይ የአገዛዙ እርምጃ የጀመረውን የኮማንድ ፖስት እዝ በማጠናከር የቅዱስ ሲኖደስ አባቶችን በማሰር፣ መላ ሀገሪቷን የጦር ቀጠና እንደሚያደርጋት ይጠበቃል። በተጨማሪም በየሚድያው ጠንከር ያለ ተቃውሞ የሠነዘሩ የፖለቲካ አባላት/መሪዎችን ጨምሮ ታዋቂ ግለሰቦችን ማሳደድ እንደሚጀምር ልንጠቁም እንወዳለን።

መኢአድ፣ እናት ፓርቲና ኢሕአፓ የጀመራችሁትን የጋራ ስምምነት ከቻላችሁ አድማሱን በማስፋት ካልሆነም እራሳችሁን በጋራ አጠናክራችሁ ትግሉን ለመምራት መዘጋጀት ይኖርባችኋል።ሰላማዊ ትግል የምርጫ ፖለቲካ ብቻ አይደለም። ሀገር ለማጥፋት መንግሥት እስከ ቀጣዩ ምርጫ ትዕግስት እንደሌለው እያሳየ ነውና ቤተክርስቲያንን የደፈረ አገዛዝ፣ ከአምላክ በላይ አዋቂ ሁኖ ፈጣሪ እያለ አምላክን የሚፈታተን ዳቢሎስ ተለቋልና ለሀገርና ሕዝብ ብላችሁ ትግል ጀምራችኋልና ከሕዝብ ጋር ሁናችሁ ታሪክ ትሰሩ ዘንድ አደራ እንላለን።

ለአማራ እልውና እየተፋለምክ ያለኸው የአማራው ፋኖ ኢትዮጵያ ትበታተን ትጠፋ ከተፈለገ በቅዠታሙ ዶር ዐብይ ሂደት አማራው ይጠፋ፣ ይቀበር ተፈርዶበታልና በአለፉት 5 ዓመት በሚሊዮን የሚቆጠሩ አማሮች ሲሰዉ በሕይወት ያሉትም በየጫካውና ዱሩ የመከራ ሕይወት ይገፋሉ። አማራው ከራሱ ዘር አሻግሮ ኢትዮጵያን ነፃ ማውጥት በእጅህ ነውና የፍልሚያው መሪ የመሆን አደራ ጊዜው ጥሎብሃል። ኦርቶዶክስ ሀገር ናት እንደተባለው ተወደደም ተጠላ አማራም ሀገር መሆኑን አሳያቸው።

የአገዛዙ የጭካኔ መጠን አድማሱን እያሰፋ ስሞኑን እየተደረገ ያለው ከአማራው ክልል ያለው የአማራ ዘር ወደ አዲስ አበባ እንዳይገባ የሚደረገው ክልከላ ምን ያህል አማሮች በየቦታው እየተጉላሉ እንደሆን መገመት አዳጋች አይደለም። ዘመድ ለመጠየቅ ሄደው ሲመለሱ እንዳይገቡ የተከለከሉ፣ ለህክምና እና ለተለያየ ጉዳይ

የሚንቀሳቀሱትን አማራ በመሆናቸው ብቻ ማሰቃየቱ ያበቃ ዘንድ አማራው አንድነቱን አጠናክሮ መፋለም ይጠበቅበታል።

በሌላ በኩል ደግሞ የሰሞኑ የውልቂጤ እልቂት በአገዛዙ ተቃውሞ በማንሳታቸው ብቻ ነዋሪውን በውሃ ለመቅጣት በተደረገው አረመኔያዊ ድርጊት ይባስ ብሎ ጀሪካን ይዘው የውጡ እናቶች እና ወጣቶች ላይ የተካሄደው አረመኔያዊ ጭፍጨፋ እጅጉን ያሳዝናል።

ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ በጥቅሉ፣ የአዲስ አበባ ሕዝብ በተለይ ለአለፉት 32 ዓመታት በዘር ፖለቲካ ሀገርና ሕዝብ ሲታመሱ ለመኖራቸው የገፈቱ ቀማሽ ከራስህ በላይ ምስክር አያስፈልግም። አሁን ደግሞ ሃይማኖትህን ሊያፈርስ፣ ሀገርህን ሊበታትን በዳቢሎስ መሪነት ኦሮሙማ በየእሥርቤቱ እያጎረህ፣ አውላላ ሜዳ ላይ ከነቤተሰብህ እያሰጣህ፣ እንደከብት እያረደህ፣ የነሱ ጀግንነት ባዶውን ያለ ሕዝብ በጥይት መፍጀት ነውና በየቀኑ እየፈጀህ፣ ልጆችህን በየትምህርት ቤቱ እያሰቃየ፣ በኑሮ ውድነት እየቀጣህ፣. . .ኸረ ስንቱ ይዘረዘራል ከዚህ በላይ ምን ልትሆን ይፈለጋል? በቃኝ! ብለህ ከተነሳህ የምትከፍለው ሕይወት ይህንን አረመኔ ቡድን ጠራርጎ ወደ ታሪክ አተላነት መክተቱ አይቀሬ ነውና ተነስ! ተዘጋጅ። በቁምህ መሞት ጀግንነት አይደለምና በደም በአጥንታቸው ሀገርና ሃይማኖት ያኖሩልህ አባቶችህና እናቶችህን ዓርማ የማንሳት ወሳኝ ወቅት ላይ ደርሰሃልና ሳታወላዳ ከተባበርህ ሀገርም ትድናለች፣ ሃይማኖትህም ይጠበቃል። በመሆኑም ሠራተኛው፣ ታክሲ ነጂዎች፣ ነጋዴዎች ሥራ በማቆም፣ መምህራንና ተማሪዎች ትምህርት በማቆም፣ ሁሉም ምግብ እና የመጠጥ ቤቶች እንዲሁም መለስተኛ ነጋዴዎች “የሙት ቀን አድማ” ለማድረግ ከተባበራችሁ ድሉ የሀገርና የሕዝብ መሆኑን አትጠራጠሩ።

በውጭው ዓለም ያላችሁ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እስከዛሬ ሳትታክቱ ለሀገራችሁና ለሕዛባችሁ ብርድና ሙቀት ሳትሉ ድምጻችሁን አሰምታችኋል። አሁንም ሀገርና ሃይማኖት ለማዳን በሚደረገው ወሳኝ ፍልሚያ ሳትታክቱ በመሰባሰብ በሀገር ቤት ለሚካሄደው እንቅስቃሴ ተገን ለመሆን ተዘጋጁ።

የመገናኛና የሚዲያ ወገኖች በአጠቃላይ በአገዛዙ ሥር ያላችሁ የሚድያ አካላት በምትሰሩት አሳፋሪ ተግባር ጊዜ ይውቀሳችሁ። ሀገራችሁ ተበትና ሃይማኖታችሁ ተራክሶ ኖርን ከሚሉ ከንቱዎች ጋር አትደረቡ። ድፍረቱን ተላብሳችሁ ለኢትዮጵያችን ድምጽ ሁኗት። በተለይ በውጭው ዓለም ነጻ ሆናችሁ የምትንቀሳቀሱ እስከዛሬም ለሀገርና ለሕዝብ ቀን ተሌት የምትለፉ ሀገርና ሕዝብ እንደሚያመሰግኗችሁ አትጠራጠሩ። አሁንም የሀገራችን ሕዝብ ሆ! ብሎ በዚህ የዳቢሎስ አገዛዝ ላይ ሕዝባዊ ቁጣውን በማጠናከር መንግሎ ይጥለው ዘንድ የአየር ሰዓት ሰጥታችሁ በየጊዜው ቅስቀሳ ማድረግ የሚገባችሁ ወቅት ላይ ናችሁና ምከሩበት።

ለብልጽግና ባለሥልጣናት በኢትዮጵያችን እንደሁሉም ዜጋ እውነተኛ ለውጥ የመጣ መስሏችሁ የሥልጣን ተቋዳሽ የሆናችሁ በሀገራችን ላይ እየተካሄደ ያለውን ዘረኛ አገዛዝ ከቀን ወደ ቀን መረን እየለቀቀ መሄዱን እየተመለከታችሁ ድምጽ አለማሰማት በታሪክ ተጠያቂ ያደርጋልና የጉዳዩ ተባባሪ ያልሆናችሁ በጋጠወጥ መሪ ቁጭ ብሎ ከመሰደብ ከሕዝብና ሀገር ወግናችሁ ታሪክ ስሩ።

ለኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ሕጻናት፣ ወጣቶች፣ አዛውንት እናት አባቶችን በዱላ መቀጥቀጥ ከዚያም አልፎ ጥይት ማርከፍከፍ እጅግ ኀሊናችሁን ሊቆጠቁጣችሁ ይገባል። የካቲት 66 ሕዝባዊ አብዮት ወቅት ለወታደሩ እንዲህ ሲባል ተገጥሞለት ነበር "ደምህ የጭቁን ደም፡አጥንትህ የምዝብር፤ ጭቁን ወታደር፡ከህዝቡ ጋር አብር" ይህ ግጥም ዛሬም ህያው ነውና ከሕዝብ አብራክ የወጣኸው የሠራዊቱ አባላት በተለይ ደግሞ የፌደራልና ክልል ፖሊስ አባለት ዱላችሁን ወደ አገዛዙ በማዞር ሕዝባችሁን አለንልህ በማለት ኢትዮጵያን ከመበታተን አድኗት።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኖራለች!

ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይባርክ!

የካቲት 11 ቀን 2015 ዓ.ም. (February 18, 2023)

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org , www.ethiopiachen.com
ምሥለ ገጽ ፡ IHIH Ethiopiachin